በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 220782

ህዳር 26 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡...

1. እትመት አሰፋ
2. ሌሊሴ ደሳለኝ
3. ደጀኔ አያንሳ
4. ሀብታሙ እርቅይሁን
5. እቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡..... 1ኛ. አቶ ሙጬ ማዘንጊያ

2ኛ. አቶ ደሴ ይርዳው

3ኛ. ወ/ሮ ይመኝ ሞላ

1ኛ አመልካች ብቻ ቀርቧል

ተጠሪ፡..... አቶ ሞገስ መንግስቱ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ በባህርዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ሰኔ 3 ቀን 2010 ዓ/ም ያቀረበው ክስ አስቀድሞ ቡተመሳሳይ ጉዳይ በዚያው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 21018 ያቀረበውን ክስ በማንሳቱ መዝገቡ ተዘግቶ እያለ ዳግም ክስ ማቅረብ የለበትም በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ መሆኑ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ የሥር የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 103879 ውድቅ በማድረግ የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ይታረምልን በማለት አመልካቾች ሐምሌ 13 ቀን 2014 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማመልከታቸው ነው።።

ተጠሪ በባህርዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ሰኔ 3 ቀን 2010 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ ግራ ቀኙ በጋራ ያቋቋሙት ወፍጮ ቤት እና መጋዘን አመልካቾች በግላቸው አከራይቶ የተጠቀሙበት ያለውን

ማሳሰቢያ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዘር አንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ድርሻቸውን ብር 11,250 (ሁለት መቶ ሃምሳ) ብር እና ቤቱ ሲሰራ የተረፈ እንጨት ግምት ድርሻቸው 375.00(ሶስት መቶ ሰባ አምስት) ብር ፡ እንዲሁም አመልካቾች ወፍጮ ቤቱን በግላቸው እየተጠቀሙ በመሆኑ በጋራ እንዲጠቀሙ እንዲወሰንላቸው ያቀረቡት ክስ ለአመልካቾች ደርሶ ባቀረቡት መልስ ክርክር እየተደረገበት ያለውን ወፍጮ ቤት የግሌ ነው በማለት ተጠሪ በዚያው ፍርድ ቤት ቁጥራቸው 21018 እና 42898 በሆነው መዝገብ ላይ ተከራይተው ክሱ የቀረበበት ወፍጮ ቤት የተጠሪ አለመሆኑን ስለተረዱ ያቀረቡትን ክስ እንስተው ኪሳራ 500.00(አምስት መቶ) ብር ከፍለው መዝገቡ ስዘጋ በጉዳዩ ላይ ዳግመኛ የመክሰስ መብት ተጠብቆ ባለመሆኑና በዚህ ክስ ላይ የቀረበው የኪሳር ክርክርም ከቀደመው ክስ ተቀንሶ የቀረበ በመሆኑ ተጠሪ አስቀድሞ ቡተወው ጉዳይ እያረፈ የመክሰስ መብት የሌለው በመሆኑ ጉዳዩ ላይ ያቀረቡት ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ /ቁ. 5,216(3) እና 244(2) መሠረት ውድቅ ነው በማለት በፍሬ ነገሩ ላይም አማራጭ ክርክር አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በአመልካቾች በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ መልስ እንዲያቀርቡ ታዘው በሰጡት መልስ፡- አስቀድሞ ያቀረቡት ክስ ወፍጮው ሲነሳ 60000.00 (ስልሳ ሺ) ብር ግምት ተቀብለዋል በማለት ወፍጮውን በመቆለፋቸው በወፍጮው ሰርቼ የማገኘው የገንዘብ ድርሻዬ እንዲሰጠኝ ያቀረቡት ክስ በክርክር ላይ ካለው የቤት ኪራይ ጋር ግንኙነት የሌለው በመሆኑ መቃወሚያው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አስቀድሞ ግራ ቀኙ ተከራክረንበታል የሚሉትን የመዝገብ ቁጥር 210818 እና 12898 ሲታይ ቤቱን ሰብረው ገብተው አከራይተው ይጠቀማሉ በሚል ቀርቦ የነበረው ክስ መቋረጡ አዲስ ክስ ማቅረብን የማይከለክል ሲሆን ሁለተኛው መዝገብ ሁከት እንዲወገድ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ ያደረገው የባህርዳር ወረዳ ከተማ ፍርድ ቤት ፡ ወፍጮ ቤቱ የሥር ተከሳሾች ባደረጉት መዋጮ በተከራካሪዎቹ የጋራ ይዞታ ላይ የተገነባ በመሆኑ ተጠሪ የቤቱን የወቅቱን ዋጋ ግምት በድርሻው ቤቱ ለሰሩት አባላት ከከፈለ በኋላ የሚገኘውን የኪራይ ጥቅም ክፍያውን ከከፈለበት ጊዜ አንስቶ ያለውን በድርሻው ማግኘት የሚችል መሆኑ እና ወፍጮውንም አብሮ መጠቀም ይችላል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች በውሳኔ ባለመስማማት አስቀድሞ በመዝገብ ቁጥር 21018 ላይ በተመሳሳይ ጉዳይ ቀርቦ የነበረው ክስ በተጸረጠበት አግባብ ዳግም ሊጠይቅ አይገባም በማለት ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው የባህርዳርና አከባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡት መቃወሚያ በሥር ፍርድ ቤት የመታለቱን አግባብነት ብቻ ለመመርመር መዝገቡ አስቀርቦ ግራ ቀኙን አከራክሮ መዝገቡን እንደመረመረው፡- ክርክሩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከወፍጮው ማግኘት የሚገባውን ገቢ እንዳያገኝ አመልካቾች ማድረግ / አለማድረጋቸው ፡ እንዲሁም ወፍጮ የተሰራው በተጠሪ ወይስ በአመልካቾች ወጪ ነው? የሚለው በመዝገብ ቁጥር 21018 ላይ ተጣርቶ ውሳኔ እንዲያገኝ ጭብጥ ይዞ በመለሰው አግባብ ክርክሩ ቀጥሎ እያለ ተጠሪ ክሳቸውን ማንሳታቸውን በመግለጽ ባቀረቡት አቤቱታ ችሎቱም 500.00(አምስት መቶ) ብር ኪሳራ ቆርጦ ኪሱ በመቋረጡ በመዝገብ ቁጥር 21018 እና በመዝገብ ቁጥር 52184 ላይ ያለው ክርክር ጭብጥ አንድ በመሆኑ ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 21018 በራሱ ፍላጎት ባቋረጠው ተመሳሳይ ጉዳይ አዲስ ክስ ማቅረብን የፍ/ሥ/ሥ/ሕ. 279(1) ይከለክላል በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡

ማሳሰቢያ፡- ይህ የህዝብ ችሎት ውሳኔ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማነጻጸሪ ለንጽጽር ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያስፈልግም

ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ ጉዳዩን የተመለከተው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 21018 አቅርቦ የነበረውን ክስ የተጻረጠው ተጠሪ ክሱ ለማጻረጥ ጠይቆ ፍርድ ቤቱም ኪሳራ ቆርጦ ክሱን እንድተው ፈቅዶለት መዝገቡን ስለተዘጋ ክሱን እንዲተው ሲፈቀድ በጉዳዩ ላይ ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል ዳግም ክስ ለማቅረብ እንደማይችል ካልተገለፀ በቀር በፍርድ ቤት ፈቃድ ክሱን የተወ ከሳሽ በጉዳዩ ላይ ዳግም ክስ ማቅረብ ይችላል ብሎ መውሰድ ስለሚቻል ፣ ተጠሪ በፍርድ ቤት ፈቃድ አስቀድሞ ክሱን ሲተው በተወው ጉዳይ ላይ በድጋሚ ክስ ማቅረብ እንደማይችል ባልተከለከለበት ሁኔታ ክስ የማቅረብ መብቱን አልተጠበቀለትም በሚል ምክንያት ተጠሪ በድጋሚ ክስ ሊያቀርብ አይችልም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ አግባብነት የለውም በማለት ውሳኔውን በመሻር በፍሬ ነገር ክርክሩ ላይ የተሰጠውን የወረዳ ፍርድ ቤት ፍርድ አግባብነት አይቶ ውሳኔ እንዲሰጥ በመመሪያ መዝገቡን ለባህርዳርና አከባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤትመልሶታል፡፡ በዚህ አግባብ መዝገቡ የተመለሰለት የባህርዳርና አከባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት የአመልካቾች የይግባኝ አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ውድወቅ አድርጎል፡፡ አመልካቾች የባህርዳርና አከባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ያቀረቡረትን የሰበር አቤቱ በፍሬ ነገር ክርክሩ ላይ የሰጠው ውሳኔ አግባብ መሆን አለመሆኑን የመረመረው የሥር የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት በሰበር ለማሳር ሆኖ የአቤቱታው ይዘት፡- ለሰበር ክርክሩ ምክንያት በሆነው ጉዳይ ላይ ግራ ቀኙ በመዝገብ ቁጥር 21018 ላይ በመከራከር ላይ እያሉ ተጠሪ ሰኔ 13 ቀን 2008 ዓ/ም ክሱ ለማንሳት አቤቱታ ሲያቀርብ ለአመልካቾች 5,000.00(አምስት ሺ) ብር ከፍሎ መዝገቡ ያለፍርድ ቤት ፈቃድ ከተዘጋ በኋላ የተዘጋው መዝገብ እንዲንቀሳቀስለት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ተብሎ የተሰጠው ብይን ባልተሸረበት ተጠሪ በዲጋሚ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት አግኝቶ ውሳኔ መሰጠቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 5 244(2) እና 279(1) ድንጋጌዎችን የጣሰ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀበት በመሆኑ ሊሻር ይግባል በማለት የፍሬ ነገር ክርክሩ በሚመለከት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት አለበት የሚሉበትን ምክንያቶች በመዘርዘር በሰበር ሰሚ ችሎቱ እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአመልካቾችን የሰበር ቅሬታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ፡- ተጠሪ አስቀድሞ ያቀረበው ክስ ያለፍርድ ቤት ፈቃድ ክሱን በማንሳቱ ኪሳራ ከፍሎ መዝገቡ በመዘጋቱ አዲስ ክስ ሊያቀርብ አይችልም በማለት አመልካቾች ያቀረቡት መቃወሚያ በሥር ፍርድ ቤቶች የታለፈበትን አግባብ ከፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 279(1) አንፃ መጣራት አለበት በማለቱ ተጠሪ በሰጡት መልስ በመዝገብ ቁጥር 21018 ላይ የነበረው ክስ ቀድሞ ቢጋራ ወፍሮ ቤት ይሰሩበት የነበረው የግል ቤት ለልማት ሲወሰድ የተሰጠው ትክ ቦታ የማሌ ነው በሚል ሲንከራከር ቆይተን አብሮነት በማሰብ ቢጋራ ለመስራት በፍርድ ቤት ፈቃድ የተዘጋው መዝገብ እና ለሰበር ክርክሩ ምክያት ከሆነው ጉዳይ ጋር አንድ አለመሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ

ማሳሰቢያ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማነጻጸሪ አንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አንድ ዓይነት ነው ቢባል እንኳን በፍርድ ቤት ፈቃድ ክስ ማንሳት በዛው ጉዳይ ክስ ማቅረብን የሚከለክል ባለመሆኑ ተጠሪ ያቀረቡት የክስ በማስረጃ ተጣርቶ የተሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም ግራቀኙ በመዝገብ ቁጥር 21018 ላይ በክርክር ላይ እያሉ ተጠሪ ጥር 13 ቀን 2007 ዓ/ም ያቀረቡት አቤቱታ ክሳቸውን ማንሳታቸውን የሚገልጽ እንጂ በተመሳሳይ ጉዳይ ክስ እንዲያቀርቡ ፍርድ ቤቱ መብታቸውን እንዲጠብቅላቸው የማያመለክት መሆኑን በመልለጽ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፊ ሲል የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም መዝገቡ ያስቀርባ ሲባል የተያዘውን ጭብጥ አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከሳሽ ባቀረበው ክስ የመቀጠል ወይንም ያለመቀጠል ፍጹም የሆነ መብት ስላለው ክርክሩን እንዳያቋርጥ ሊገደድ አይገባም፡፡ ክሱን የማቋረጥ ውጤት ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል በተቋረጠው ጉዳይ አዲስ ክስ የማቅረብ መብቱን ስለሚያሳጣው ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል በተቋረጠው ጉዳይ አዲስ ክስ ለማቅረብ ክሱ በፍርድ ቤት ፈቃድ መቋረጥ አለበት፡፡ ያለ ፍርድ ቤት ፈቃድ ክስ መቋረጥ ኪሳራ መክፈልን ሊያስከትል የሚችል ከመሆኑን በላይ ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል በተቋረጠው ክስ አዲስ ክስ የማቅረብ መብትንም ያሳጣል፡፡ በፍርድ ቤት ፈቃድ የተጀመረውን ክስ ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ሊኖር እንደሚገባ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 278(2) ይደነግጋል፡፡

ክስ እንድቋረጥ መፍቀድ ለፍርድ ቤት የተሰጠ ፍቅድ ሥልጣን(discretion of the court) በመሆኑ ፍርድ ቤት የክስ አቀራረብ ሥርዓት ጉድለት መኖሩን ሲረዳ በራሱ ጊዜ አልያም ከሳሹ ክሱን ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል ለማቋረጥ የሚያስችል በቂ ምክያት ኖሮት አቤቱታ ለፍርድ ቤት ባቀረበ ጊዜ ፈቃዱ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ክስ ለማቋረጥ የሚያስችል ፈቃድ የማግኘት ውጤቱ አስቀድሞ በጉዳዩ ላይ ምንም ክስ እንዳልቀረ ተወሰዶ ለከሳሹ አዲስ ክስ የማቅረብ ነፃነት ስለሚሰጠው ከዚህ አንፃር ቡተከሳሽ ሊቀርብ የሚችለውን መቃወሚያ ያስቀርለታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በመዝገብ ቁጥር 21018 ላይ ቀርቦ የነበረው ክስ እና ለሰበር ክርክሩ ምክንያት በሆነው በመዝገብ ቁጥር 52184 የቀረበው ክስ አንድ መሆኑን የክሶቹን ይዘት የተመለከቱት የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡ ፍሬ ነገር በመሆኑ ተጠሪ በሁለቱ መዛግብት የቀረቡ ክሶች አንድ አይደሉም በማለት ተጠሪ የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በሁለቱም ጊዜ የቀረቡ ክሶች አንድ መሆናቸው ከተረጋገጠ ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 21018 ላይ ያቀረቡት ክስ ያቋረጡት በፍርድ ቤት ፈቃድ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መመርመር ተገቢ ነው፡፡ አመልካቾች ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 21018 ያቀረቡትን ክስ አንስተው ኪሳራ 500.00(አምስት መቶ) ብር ከፍለው መዝገቡ ስዘጋ በጉዳዩ ላይ ዳግመኛ የመክሰስ መብት ተጠብቆላቸው ባለመሆኑ አስቀድሞ በፈቃዳቸው በተውት ጉዳይ ላይ ዳግም ክስ ሊያቀርቡ አይገባም በማለት ላቀረቡት ክርክር ተጠሪ አስቀድሞ ክስ የተቋረጠበት ጉዳይ እና ለሰበር ክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ አንድ አይደሉም ከማለት በለፈ የቀደመው ክስ በፍርድ ቤት ፈቃድ ተቋርጦ አዲስ ክስ እንዲያቀርቡ የተጠበቀላቸውን መብት መሠረት አድርጎ የቀረበ ክስ መሆኑን ግልጽ ክርክር አላቀረቡም፡፡ የባህርዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በሁለቱ መዛግብት የቀረቡት ክሶች አንድ አይደሉም በማለት መቃወሚያውን ውድቅ ያደረገ ቢሆንም ፡ ጉዳዩን

ማሳሰቢያ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ ለንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በይግባኝ ያየው የባህርዳርና አከባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱ የተጻረጠው ተጠሪ ክሳቸውን ለማጻረጥ ባቀረቡት አቤቱታ 500.00(አምስት መቶ) ብር ኪሳራ ተቆርጦ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 279(1) መሠረት በተመሳሳይ ጉዳይ አዲስ ክስ ለማቅረብ አይችሉም በማለት ወስኗል፡፡

ይግባኝ ሰሚው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የባህርዳርና አከባቢዋን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን የሻረው በመዝገብ ቁጥር 21018 ክስ የተጻረጠው ተጠሪ ክሱ ለማጻረጥ ጠይቆ ፍርድ ቤቱም ኪሳራ ቆርጦ ክሱን እንድተው ፈቅዶ መዝገቡ ስለተዘጋ ፡ ክሱን እንድተው ሲፈቀድ በጉዳዩ ላይ ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል ዳግም ክስ ለማቅረብ እንደማይችል ካልተገለፀ በቀር በፍርድ ቤት ፈቃድ ክሱን የተወ ከሳሽ በጉዳዩ ላይ ዳግም ክስ ማቅረብ ይችላል ብሎ መውሰድ ይቻላል በሚል ምክንያት ነው፡፡ ከሳሽ ክሱን ለመተው(ለመጻረጥ) የራሱ ውሳኔ እንጅ የፍርድ ቤት ፈቃድ አያስፈልገውም፡፡ ክስ ለማጻርጥ ብቻ በሚል ለፍርድ ቤት የሚቀርብ አቤቱታ ክሱ በተጻረጠበት ጉዳይ ዳግም የመክሰስ መብትን የሚያሰጥ አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቱ ከሰጠው ምክንያት መረዳት የሚቻለው ተጠሪ ክስ ለመተው ፈቃድ መጠየቃቸውን እንጅ ክሱን በፍርድ ቤት ፈቃድ ለመጻረጥም በቂ ምክንያት ኖሯቸው ፡ ፍርድ ቤቱም የቀረበውን ምክንያት መርምሮ ክሱ ባጻረጡበት ጉዳይ ዳግም ክስ ማቅረብ የሚያስችላቸውን ፈቃድ አለማግኘታቸውን ነው፡፡

ከሰበር አቤቱታ ጋር ተያይዞ ከመጣው የመዝገብ ቁጥር 21018 ግልባጭ መረዳት እንደተቻለው ተጠሪ ጥር 13 ቀን 2007 ዓ/ም ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት በክሳቸው መቀጠል የማይፈልጉበትን ምክንያት በማለጽ ክሳቸውን በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 278(1) መሠረት ስላነሱ ክሱ እንዲነሳ እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው ፡ ፍርድ ቤቱም በተጠሪ አቤቱታ ላይ አስተያየት ከሳጠ በኋላ አመልካቾች ክሱ መነሳት የለበትም በማለት የተቃወሙ ቢሆንም ከሳሽ በማንኛውም ጊዜ ክሱን ሊያነሳ ሰለሚችል ክሱን እንዲያነሳ መፍቀዱን ገልፆ ፡ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 279(1) መሠረት ክስ ሲነሳ ኪሳራ መክፈል ያለበት በመሆኑ ተጠሪ 5,000.00(አምስት ሺ) ብር ኪሳራ ሊከፍል ይገባል በማለት ጥር 29 ቀን 2007 ዓ/ም መዝገቡን የዘጋ ሲሆን ፡ መዝገቡ በዚህ አግባብ ከዘጋ በኋላ ተጠሪ የተዘጋው መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ ፡ ክሴን አንስቻለው በሚል አቤቱታ ለአመልካቾች ኪሳራ ተወስኖ በተጻረጠ ክስ መዝገቡ ሊንቀሳቀስ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ገልፆ አቤቱታው ውድቅ አድርጓል፡፡

ሲጠቃልል ተጠሪ መዝገብ ቁጥር 21018 አቅቦ የነበረውን ክስ በራሳቸው ፈቃድ አንስቻለሁ በማለት አቤቱታ አቅርበው መዝገቡን ማዘጋታቸው የተረጋገጠ ሲሆን ፤ በዚህ መልክ በተውት ነገር አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚችሉበት መብት ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 278(2) ድንጋጌ መሠረት እንዲፈቀድላቸው አቤቱታ አቀርብው የተፈቀደላቸው ሰለመሆኑ ያቀረቡት ግልጽ ከርከር የሌሰ ሲሆን ፤ የሥር ፍርድ ቤቶችም ውሳኔም ተጠሪ በበቂ ምክንያት በመዝገብ ቁጥር 21018 አቅርቦ የነበረው ክስ ተጽርጦ በጉዳይ ላይ አዲስ ክስ የማቅረብ መብት የተጠበቀላቸውን መሆኑን ስለማያመለክት ተጠሪ ያለፈቃድ በተውት ጉዳይ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 279(1) መሠረት ሌላ ክስ ማቅረብ የማይችሉ ሆኖእያለ ተጠሪ በራሰቸው ፈቃድ በተውት ጉዳይ ላይ

ማሳሰቢያ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ ለንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በባህርዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 52184 ላይ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት አግኝ ውሳኔ መሰጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በመ.ቁ.103879 ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል።
2. አመልካች የመዝገብ ቁጥር 21018 ያቀረቡትን ክስ ያለፍርድ ቤት ፈቃድ በራሳቸው ሲላጵረጡ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በመዝገብ ቁጥር 52184 ያቀረቡት ክስ ዳግም የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ተወስኗል
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
4. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክሩ ያስከተሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ።

የማይነበብ የአምሰት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማሳሰቢያ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለጉድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ ለንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም